


## የተመረጠ አገልግሎት ምዝገባ (Selective Service Registration)፡ የተለመዱ ጥያቄዎች መልሶች

### [ጥ] ማን ነው መመዝገብ ያለበት?

[መ] የፌደራል ሕግ ከ18 እስከ 26 ዓመት ያሉ እና በአሜሪካ የሚኖሩ *ሁሉም* ወንዶች ለተመረጠ አገልግሎት ምዝገባ ዘዴ እንዲመዘገቡ ያዛል፡፡ ይህም የስደተኝነት ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን ዜጋ ያልሆኑ እና ሁለት ዜግነት ያላቸውን ሰዎች ያካትታል፡፡ ዜጋ ያልሆኑ እና የተማሪ ወይም የጉብኚ ቪዛ ያላቸው ወይም የዲፕሎማሲያዊ ወይም የንግድ ተልዕኮ አካላት የሆኑት ግለሰቦች ብቻ ናቸው የሚታለፉት፡፡

### [ጥ] ወንዶች መቼ ነው መመዝገብ ያለባቸው?

[መ] ከ18 እስከ 26 ዓመት ዕድሜ ውስጥ ያለ እና በአሜሪካ ውስጥ ከ30 ቀን በላይ የኖረ ማንኛውም ወንድ መመዝገብ አለበት፡፡ አንድ ወንድ አሜሪካ ውስጥ እየኖረ 18 ዓመት ከሞላው በልደቱ በ30 ቀናት ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡ ግለሰቡ 26 ዓመት እስኪሆነው ድረስ ዘግይቶ እንዲመዘገብ ይፈቀድለታል፡፡

### [ጥ] ዜግነት የማግኘት ብቁነት ከተመረጠ አገልግሎት ምዝገባ ጋር ይገናኛል?

[መ] ዜጋ ለመሆን የሚፈልጉ ስደተኛ ወንዶች ከ18 እስከ 26 ዓመት ዕድሜ ውስጥ ካሉ እና በአሜሪካ ውስጥ ከ30 ቀን በላይ ከኖሩ ለተመረጠ አገልግሎት ምዝገባ መመዝገብ አለባቸው፡፡ አንድ ወንድ 31 ዓመት ከሆነው በኋላ የተመረጠ አገልግሎት ለዜግነት መስፈርት አይሆንም፡፡ ነገር ግን በርካታ ሌሎች ጠቃሚ እድሎች ከምዝገባው ጋር ይያያዛሉ፡፡

### [ጥ] ሌሎች ምን ዓይነት ዕድሎች ከምዝገባ ጋር ይያያዛሉ?

[መ] እንዲመዘገቡ የሚፈለግባቸው ነገር ግን ያልተመዘገቡ ወንዶች ለተወሰኑ ዕድሎች ብቁ **አይሆኑም**፡፡ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል:

- ✓ የፌደራል ተማሪዎች ብድር;
- ✓ በፌዴራል ደረጃ የገንዘብ ዕርዳታ ለሚደረግባቸው የስራ ስልጠና መርሃ ግብሮች መመደብ;
- ✓ ፌዴራል መንግስት፣ በርካታ የክልል እና የአካባቢ የመንግስት ኤጀንሲዎች እና አንዳንድ የግል ቀጣሪዎች ጋር ስራ ማግኘት; እና
- ✓ በአብዛኛዎቹ ክልሎች (ስቴቶች) ውስጥ መንጃ ፈቃድ ማግኘት እና ማሳደስ፡፡

በ26ኛ ዓመት የልደት በዓላቸው ላይ ሳይመዘገቡ የቀሩ ወንዶች እነዚህን ዕድሎች **በቋሚነት ሊከለከሉ ይችላሉ**፡፡ በተጨማሪም ሕጉ እንደሚደነግገው ያልተመዘገቡ ወንዶች እስከ $250,000 ድረስ ቅጣት እና እስከ አምስት አመት የሚደርስ እስር ሊገጥማቸው ይችላል፡፡

### [ጥ] ወንዶች እንዴት መመዝገብ ይችላሉ?

[መ] የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር ያላቸው ወንዶች በመረጃ መረብ (ድረ ገጽ) www.sss.gov ላይ መመዝገብ ይችላሉ፡፡ የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር የሌላቸው ወይም ኮምፒዩተር ማግኘት የማይችሉ ወንዶች፣ ከማንኛውም የአሜሪካ ፖስታ ቤት የምዝገባ ቅፅ ወስደው በመሙላት መመዝገብ ይችላሉ፡፡

### [ጥ] ይህ የተመረጠ አገልግሎት ዘዴ የውትድርና አካል ነው?

[መ] አይደለም፡፡ የተመረጠ አገልግሎት ዘዴ ሲቪላዊ ተቋም ነው፡፡ የተመዘገቡ ወንዶች ለውትድርና እንደተመዘገቡ **አይቆጠርም**፡፡

### [Q] የበለጠ መረጃ ከየት ማግኘት እችላለሁ?

[A] ስለተመረጠ አገልግሎት ምዝገባ ተጨማሪ መረጃ www.sss.gov ላይ ይገኛል፡፡